# የሥነ ጥበብ ትምህርት

## 8ኛ ክፍል

## ማውጫ

*መግቢያ* ...........................................................................................
አጠቃላይ አላማዎች.......................................................................................
የ8ኛ ክፍል የሥነ ጥበብ ትምህርት የክፍለ ጊዜ ድልድል ........................................
ማሳሰቢያ ...........................................................................................
ምዕራፍ አንድ - የሥነ ጥበብ ታሪክ ..........................................................
ምዕራፍ ሁለት - ንድፍ/ዲዛይን/...................................................................
ምዕራፍ ሶስት - ቀለም ቅብ .....................................................................
ምዕራፍ አራት - ህትመት...........................................................................
ምዕራፍ አምስት - ኪነጽህፈት ......................................................................
ምዕራፍ ስድስት - ቅርጻ ቅርጽ ....................................................................
ምዕራፍ ሰባት - ኮምፒውተር ግራፊክ ...........................................................

## መ ግ ቢ ያ

ይህ የ8ኛ ክፍል የሥነ ጥበብ ትምህርት መርሀ ትምህርት በአዲስ መልክ ወቅታዊ የሆኑ የልማትና የዲሞክራሲ መርሆዎችን በመተግበርና የኤች. አይ.ቪ. ኤድስንና ሌሎች ተዛማጅ የጤና ችግሮችን በማካተት ከ5-6 የነበረውን የትምህርት አሰጣጥ በማፍታታትና ጫናውን በማቃለል እስከ 8ኛ ክፍል ቀጣይነት እንዲኖረው ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

ዓላማውም ተማሪዎች በስዕልና ቅርፃ ቅርጽ ዲዛይንና በፈጠራ ጥበብ አማካኝነት የራሳቸውን ስሜትና ፍላጎት ካለተፅዕኖ ለመግለፅና የፈጠራ ችሎታቸውን ይበልጥ ለማዳበር የሥነ ጥበብና እደ ጥበብ ምንነትን የሚገነዘቡበት እና እንዲሁም ውጤቶቻቸውን ለዲዛይንና ቴክኒዎሎጂ የማእዘን ደንጊያ መሆናቸውን አውቀው በማድነቅ መጠበቅ የሚችሉበትን ዕውቀት ለማስጨበጥ ነው።

መሠረታዊ የሆኑ የሥነ ጥበብ ባህርያትን ለማስገንዘብ ይሰጡ የነበሩት የሁለት ክፍል ትምህርት ሁሉንም የጥበቡን እውቀት በመሠረታዊነት ለማስጨበጥ ጫና የበዛበትና በቀጣዩ የትምህርት ሥርዓት በኮሌጆች ደረጃ ለሚሰጠው ትምህርት ያለውን ክፍተት ለማጥበብ ትምህርቱ እስከ 8ኛ ክፍል መቀጠሉ ተገቢነትና ተያያዥነት እንዲኖረው ያደርገዋል።

በመሆኑም የትምህርቱን አሰጣጥ ከቀላል ወደ ከፍተኛ /ዝርዝር/ ትምህርት ለማዳረስ ታስቦ ተከታታይነት ባለው መልኩ ተዘጋጅቷል።

በዚሁ መሠረት በዚህ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች በአስተሳሰብ ብስለታቸው፣ በግንዛቤ መዳበር መጀመራቸው ፣ በአካል ጥንካሬያቸው እድገት እያገኙ የሚመጡበት ጊዜ በመሆኑ የሥነ ጥበብ ትምህርቱን ይዘቶችንና የአሰራር ልምዶችን አጠናክሮ በማቅረብ የበለጠ የችሎታ የልምድና የባህርይ ለውጥ እንዲያገኙ ለማድረግ ያስችላል።

የሥነ ጥበብ ምሁራንና የሥነ ልቦና ተማሪዎች እንደሚሉት በዚህ የዕድገት ደረጃ የደረሱ ሕፃናት ሀሳባቸውን በስዕል ሥራ ከመግለፃቸውም በላይ ሰዎች ምን እንደሚያስቡ ነቅተው ስለሚጠባበቁ የመምህራኖቻቸውንና የሥዕል ችሎታ /ዲዛይን / ያላቸውን ሰዎች የመንፈስ ድጋፍና የቴክኒክ እርዳታ ይፈልጋሉ። በሥነ ጥበብ ትምህርታቸው አማካኝነት የሥነ ውበትን ሚስጥር በይበልጥ መገንዘብ ይጀምራሉ። በኑሮአቸውም ሆነ በአካባቢያቸው ያሉትን ነገሮች ስለተፈጥሮአቸውና ስለ አሠራራቸው በደረጃቸው በመመራመርና በተግባር በመተርጎም አንድን ነገር የመሥራትና የመፍጠር ልምድ መሠረት ለማግኘት ይሞክራሉ።

መምህራን ይህንኑ የተማሪዎችን አስተሳሰብና ፍላጎት በሚገባ በመረዳት ተማሪዎች የሚያገኙት ዕውቀት፣ ችሎታና የባህርይ ለውጥ በፈጠራ ጥበባቸው ለሁለገብ ዜግነት ራሳቸውን የሚያዘጋጁና ስለዲሞክራሲያዊ ህብረተሰብ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ህይወት ንቁ ስሜት ሊኖራቸው ይችላል።

በዚህ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን በዕውቀት፣ በችሎታና ፣ በባህርይ ለውጥ ፣ ለሚቀጥሉት ክፍሎች ዝግጁ ሆነው እንዲገኙ የሚያስችላቸውን አጠቃላይ አላማዎችን በዝቅተኛ ደረጃ የሚጠበቅ ውጤት ይዘቶች የመማር ማስተማር ክንውን ግምገማና የመማር ማስተማሪያ መሳሪያዎች በሚመለከተው ሁኔታ ቀርበዋል።

## የ8ኛ ክፍል የሥነ ጥበብ ትምህርት

አጠቃላይ አላማዎች

ተማሪዎች የ8ኛ ክፍል የሥነ ጥበብ ትምህርትን ሲያጠናቅቁ፡

- የብሔር ብሔረሰቦችን የሥነ ጥበብና የዕደ ጥበብ ታሪክን ይገነዘባሉ፡
- በራሱ የሚተማመን ሀገሩን የሚወድ ብቁ ዜጋ እንዲሆን ያስችለዋል፡
- ቅርስን የመንከባከብና ለትውልድ የማስተላለፍን ልምድ ያዳብራሉ፡
- ህይወት ያላቸውንና የሌላቸውን በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን ምስላቸውን በሥነ ጥበብ አማካኝነት የመግለፅን ክህሎት ያሻሽላሉ፡
- በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ነገሮች ላይ የሚታዩትን ቀለሞች ለይቶ በማውጣት የቀለሞችን መገኛ ምንጭ ይረዳሉ፡
- በማህበራዊ ኑሮ መሠረት ርዕስ ላይ የተመሰረቱ ለራሱና ለህብረተሰብ ጠቃሚ የሆኑ የሥነ ጥበብ ሥራዎችን በመሥራት የፈጠራ ችሎታቸውን ያሻሽላሉ፡
- በራሳቸው ደረጃ ዲዛይኖችን ከቀላል ቁሳቁስ በመሥራት ችሎታቸውን ያሻሽላሉ፡
- የፎቶግራፍ፣ የቪዲዮ ፣ የኮምፒዩተር ጥበብ ክህሎታቸውን ከሚሰሯቸው የሥነ ጥበብ ሥራዎች ጋር እያጣመሩ የመሥራት ልምድና ተነሳሽነት ያሳያሉ።

## የ8ኛ ክፍል የሥነ ጥበብ ትምህርት የክፍል ጊዜ ድልድል

| | | |
|---|---|---|
| ክፍለ ትምህርት አንድ | የሥነ ጥበብ ታሪክ | 2 ክፍለ ጊዜ |
| ክፍለ ትምህርት ሁለት | ንድፍ | 2 ክፍለ ጊዜ |
| ክፍለ ትምህርት ሶስት | ቀለም ቅብ | 2 ክፍለ ጊዜ |
| ክፍለ ትምህርት አራት | ህትመት | 2 ክፍለ ጊዜ |
| ክፍለ ትምህርት አምስት | ኪነ ጽህፈት | 2 ክፍለ ጊዜ |
| ክፍለ ትምህርት ስድስት | ቅርፃ ቅርጽ | 2 ክፍለ ጊዜ |
| ክፍለ ትምህርት ሰባት | ኮምፒዩተር ግራፊክስ | 4 ክፍለ ጊዜ |

# ማ ሳ ሰ ቢ ያ

## የ8ኛ ክፍል የሥነ ጥበብ ትምህርት መርሐ ትምህርት አጠቃቀም

በዚህ መርሐ ትምህርት ለሁሉም ክፍለ ትምህርቶች የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ሁለት ሁለት ብቻ ሲሆን ለግራፊክስ አርት ግን አራት ነው። የሥነ ጥበብ ትምህርት በባህሪው ቦታና በቂ ጊዜ የሚያስፈልገው መሆኑ የማይካድ ቢሆንም አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ትምህርት ቤቶቻችን ካላቸው የክፍል አደረጃጀት አኳያ በክፍል ውስጥ ትምህርቱን ለማለማመድ አመቺ አይሆንም።

በመሆኑም ለ8ኛ ክፍል የተመረጠው ዘዴ አንድ ክፍለ ጊዜ መምህሩ የተሰጠውን ክፍለ ትምህርት ገለፃ የሚያደርግበት ሲሆን ሌላው ክፍለ ጊዜ ደግሞ ተማሪዎች በተሰጣቸው ገለፃና ምልከታ በመታገዝ እቤታቸው የሰሯቸውን ሥራዎች ወደ ክፍል አምጥተው የሚያሳዩበት ይሆናል።
ይህ ዘዴ " Project –based Learning" ወይም ዕቅድ ተኮር የመማር ዘዴ የሚባለው ነው። ጥቅሙም ፡

- ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ይማማራሉ
- ለሚሰሩት ሥራ ሙሉ ኃላፊነትን ይወስዳሉ
- የሚሰሩትን ሥራ በጥልቀት ያያሉ
- የሰሩትን ሥራ ዋጋ የመስጠትና የመገምገም ልምዳቸው ይዳብራል።

ስለዚህ መምህሩ በሚያስተምርበት ወቅት ገለፃውን በተያዘለት ክፍለ ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅና በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች የቤት ሥራቸውን አምጥተው እንዲያሳዩ ማበረታታት ይኖርበታል።

## ምዕራፍ አንድ ፡ የሥነ ጥበብ ታሪክ *(2 ክፍለ ጊዜ)*

***የምዕራፉ ዓላማዎች:-*** ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ

- ታዋቂ የሥነ ጥበብ ሥራዎችንና ጥበቦችን ያውቃሉ
- የዘመናዊ ዘመን የጥበብ ታሪክ የደረሰበትን ያውቃሉ
- በየዘመናቱ የተነሱትን የጥበብ አቅጣጫዎች ያላቸውን ባህሪ ይገነዘባሉ፡፡

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| ተማሪዎች ይህን ይዘት ከተማሩ በኋላ<br>• የዘመናዊ ዘመን የጥበብ ደረጃ የደረሰበትን ይናገራሉ፡፡<br>• የጥበብ ዘዴዎች እንዴት እንደሚነሱና እንዴት እንደሚከስሙ ያውቃሉ፡፡<br><br>• በዘመናዊው ዘመን የጥበብ ታሪክ ውስጥ ብዙ አዳዲስ የአሰራር ስልቶች የመብዛታቸውን ያህል ብዙ ታዋቂ የጥበቡ ሰዎች እንዳሉ ይገልፃሉ፡፡ | **1.1.የዘመናዊ ዘመን ጥበብ**<br>*/1 ክፍለ ጊዜ/*<br>• ዘዴዎች /አቅጣጫዎች/<br><br>**1.2. ታዋቂ የሥነ ጥበብ ሰዎችና ስራዎቻቸው** */1 ክፍለ ጊዜ/* | • ተማሪዎች በዘመናዊ ዘመን ስላሉት የጥበብ ሥራዎች የሚውቁትን ያህል እንዲገልፁ ማድረግ፣<br>• ስለ ዘመናዊ ዘመን የጥበብ እድገትና በዚህ ዘመን ያሉ የጥበብ ስራዎች አይነታቸውና ሰያሜያቸው የበዛ መሆኑን ገለፃ ማድረግ፣<br>• የዚህ ዘመን የጥበብ እንቅስቃሴ ካለፉት ዘመናት ከነበረው የጥበብ እንቅስቃሴ ጋር ሲነፃፀር እጅግ በጣም ፈጣን ለውጥ እያሳየ መሆኑን ገለፃ ማድረግ፡፡<br>• ዘዴዎች እንዴት ሊነሱ እንደሚችሉና ከተነሱ በኋላ ሊኖራቸው የሚችለው ቆይታ የሚወሰነው ማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ተቀባይነትና ብዙ ተከታዮች ማፍራት የቻለ እንደሆነ ማስረዳት፣<br>• በዚያው ዘመን ያሉ ሌሎች የጥበብ ሰዎች አዲስ አይነት ፍልስፍና ወይም የአሰራር አቅጣጫ ማሳየት ሲጀምሩ የነበረውን መነሻ በማድረግ ወይም አዲስ የአሰራር ዘዴን ሲያሳዩና ተከታይ አፍርተው በማህበረሰቡ ውስጥ ሲለመድ አዲስ አቅጣጫ ማግኘት እንደሚቻል ማስረዳት፡፡<br>• ሌላው ጠቢቡ በራሱ በተሰማው መልኩ ሀሳቡን ገልጾ ቢያልፍም ማህበረሰቡ ላይረዳው ላይቀበለው ይችላል፡፡ ከዘመን በኋላ የጥበብ ሀያሲያን በሚሰጡት ጥናታዊ ትንታኔ ኢዝሞች እንደሚፈጠሩ ሰፋ ያለ ገለፃ ማድረግ፡፡<br>• በዘመናዊው ዘመን ከላይ ባሉት ክፍለ ትምህርቶች ብዙ አቅጣጫዎች ሊፈጠሩ እንደቻሉ የተረዱ ሲሆን በነዚህ በርካታ አቅጣጫዎች ውስጥ መስራቾችና ይበልጥ ታዋቂ የሆኑ የጥበቡ ባለቤቶች መኖራቸውን መግለጽ፣ የሰሯቸውን ስራዎች ይከተሉት የነበረውን አቅጣጫ እንዲገነዘቡት ገለፃ ማድረግ፡፡ |

## ግምገማ

- ስለዘመናዊ ዘመን የጥበብ ታሪክ መረዳታቸውን በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ
- ስለ ዘዴዎች አሰያየም ስለዘዴዎች ባህሪይ የተረዱትን በመጠየቅ ማረጋገጥ
- የዘመኑን ታዋቂ የጥበብ ሰዎች እንዲገልፁና ስለሰሯቸው ስራዎች መግለፃቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ

## የመማር ማስተማር መሳሪያዎች

- የሥነ ጥበብ ማስተማሪያ መፃህፍት
- የሥነ ጥበብ ታሪክ መጻህፍት
- የህትመት ውጤቶች

## ምዕራፍ ሁለት ፣ ንድፍ *(2 ክፍለ ጊዜ)*

***የምዕራፉ ዓላማዎች:-*** ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ

- የዲዛይን መሠረታዊ ነገሮች የሆኑትን መስመርን ፣ ቅርፅን፣ ቀለምን ፣ቴክስቸርን፣ ቦታን ፣ ባህሪቸውን ፣ ለይተው ያውቃሉ
- የዲዛይን መሠረታዊ መመሪያዎች የሆኑትን አንድነት /ዩኒቲ/ ፣ መጠን /ኘሮፐርሽን/ ፣ ምት /ሪትም/፣ ሚዛን /ባላንስ/ ፣ ያላቸውን ፀባይ ይገነዘባሉ።
- የዲዛይን መሠረታዊ ነገሮችን ተጠቅሞ ንድፍ በመሥራት ቁሳቁስ አሰራርን፣ አልባሳት አሰራርን ፣መልክዓ ምድር መስራትን ይችላሉ
- ከህሳብ የንድፍ ጥናት በማድረግ የተለያዩ የፈጠራ ስራዎችን በመሥራት ያሳያሉ።

| *የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘት* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ይዘት ከተማሩ በኋላ*<br>• የዲዛይን መሠረታዊ ነገሮች የሆኑትን የመስመርን ፣ ቅርፅን፣ ቀለምን ፣ቴክስቸርን፣ ቦታን ፣ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ይለያሉ። | 2.1. **የዲዛይን መሠረታዊ ነገሮች**<br>*/1 ክፍለ ጊዜ/*<br>• መስመር<br>• ቅርፅ<br>• ቀለም<br>• ቴክስቸር<br>• ቦታ | • የዲዛይን ባህሪይ ምን እንደሚመስል በመጠየቅ የእለቱን ትምህርት መጀመር። ተማሪዎቹ የሚሰጡትን ምላሽ መነሻ በማድረግ ዲዛይን በውስጡ ሊይዛቸው የሚችለውን የተለያዩ ክፍሎች በዘርፍ በዘርፋቸው እየለዩ ማስረዳት፡<br>• መስመር በዲዛይን ውስጥ ያለውን ትልቅ ቦታ ገለፃ ማድረግ፡ ለዲዛይን የምንጠቀምባቸው መስመሮች ለንድፍ ስራ ከምንጠቀምባቸው መስመሮች የሚለይበትን ባህሪ እንዲለዩ ማድረግ፡<br>• በዲዛይን ውስጥ ቅርፅ የሚኖረውን ቦታ እንዲለዩ ማድረግ ፣ አንድ ቅርጽ ወይም ምስል በተደጋጋሚ ያንኑ መጠንና ቅር ይዞ ቢቀመጥ /ቢደረደር የሚፈጥረውን የፓተርን ስሜት ምን እንደሚመስል ማሳየት፡<br>• ቀለማት በዲዛይን ሥራ ውስጥ ያላቸው ዋጋ ከመደበኛው የቀለም ቅብ ስራ እንደሚለይና በተወሰኑ ቀለማትና የቀለማት ቶን እንደሚሰራ በአቀባብም ሆነ በአቀማመጥ እንዲለዩ ማድረግ። |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| • የዲዛይን መሠረታዊ ነገሮችን ተጠቅመው ቁሳቁስ ፣ አልባሳትና መልክአ ምድር ሠርተው ያሳያሉ። | 2.2. **የዲዛይን መሠረታዊ ነገሮች ተጠቅሞ ንድፍ መሥራት** *(1 ክፍለ ጊዜ/*<br>• ቁሳቁስ<br>• አልባሳት<br>• መልክአ ምድር | • ቴክስቸር በዲዛይን ስራ ውስጥ በልስላሴና ሻካራነት የአንድን ነገር /ምስል/ ለይተው የሚሰሩበትና ለሚሰሩት ስራ እንደየባህሪው በማስቀመጥ የተፈለገውን ስሜት እንዲሰጥ ማድረግ መቻላቸውን ማሳወቅ።<br>• ቦታን በዲዛይን ውስጥ እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ማሳየት። በአንድ ምስል /ዲዛይን/ና በሌላ ምስል /ዲዛይን/ መሀል የሚኖረው ስፋት ፣ ርቀት፣ መጠን … የመሳሰሉት በቅርጽ ፣ በመጠን እኩል እንድንደረድራቸው ማስቻሉንና እይታችን የተሟላ እንዲሆን የሚያስችለን መሆኑን ግንዛቤ ማስያዝ።<br>• የዲዛይን መሠረታዊ መመሪያ የሆኑትን አራቱን ባህሪያት በተናጠል በማስረዳት አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ።<br>• ቁሳቁስን በሚሰሩበት ጊዜ ፣ አልባሳትን በሚሰሩበት ጊዜ ፣ መልክአ ምድርን በሚሰሩበት ጊዜ ፣ በሚሰሯቸው ነገሮች ውስጥ የሚኖሩትን ድግግሞሽ /ምት/ ቀለማት ፣ መጠን ቅርፅ፣ ቦታ፣ አያያዝ ፣ … የመሳሰሉትን በተገቢው ቦታ መቀመጣቸውንና ተገቢውን ባህሪይ መግለጽ መቻላቸውን ለይተው እንዲሰሩ ማድረግ። |

### ግምገማ

- የዲዛይን መሠረታዊ ነገሮች የሆኑትን መለየታቸውን በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ። በተግባር የሰሩትን በምልከታ ማረጋገጥ።
- የዲዛይን መሠረታዊ ነገሮች ተጠቅመው የሰሯቸውን ሥራዎች በምልከታ ማረጋገጥ

### የመማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎች

- የዲዛይን መሰረታዊ ነገሮችን ለመሥራት ወረቀት፣ እርሳስ፣ ላጲስ ፣ ቀለም ፣ ብሩሽ፣ የተሰሩ ናሙና ስራዎች መጠቀም
- ዲዛይንን ለመሥራት ለምንጠቀምባቸው መመሪያዎች የተሰሩ ምስሎች ፣ መፃህፍት፣ … /ስላይድ

## ምዕራፍ ሶስት፡ ቀለም ቅብ *(2 ክፍለ ጊዜ)*

***የምዕራፉ ዓላማዎች***:- ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ

- ለቀለም ቅብ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁስን አዘገጃጀትና አጠቃቀም ያውቃሉ
- የቀለም ቅብ አሰራር አይነቶችን ያውቃሉ
- የቀለማትን ቶን /ፐርስፔክቲቭ/ይረዳሉ
- የቀለም ድርሰትን ይለያሉ
- ነፃ የፈጠራ አሰራርንና ፤ የስዕል አያያዝና አጠባበቅን ያውቃሉ።

| *የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘት* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ይዘት ከተማሩ በኋላ*<br>• ለቀለም ቅብ ሥራ አስፈላጊ የሆኑትን መሥሪያ ቁሳቁስ ያውቃሉ፣ ያዘጋጃሉ ፣ አጠቃቀሙንም ይለያሉ።<br>• ስለ ቀለም ቅብ የአሠራር አይነቶች፡<br>• ስለ ውሀ ቀለም<br>• ስለ ዘይት ቀለም<br>• ስለ ቴምፕራ ቀለም ባህርይና አሰራር ይናገራሉ። | 3.1. **ለቀለም ቅብ አስፈላጊ መሳሪያዎች አዘገጃጀትና *አጠቃቀም*** */1 ክፍለ ጊዜ/*<br><br>3.2. **የቀለም ቅብ አሠራር አይነቶች** */1 ክፍለ ጊዜ/*<br>• ውሀ ቀለም<br>• ዘይት ቀለም<br>• ቴምፕራ | • አንድን ቀለም ቅብ ለመሥራት ምን ምን ቁሳቁስ እንደሚጠቀሙና እንዴት እንደሚያዘጋጁ በመጠየቅ መጀመር፡<br>• እንደሚጠቀሙት የቀለም አይነት የተለያዩ መሥሪያ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት እንዳለባቸው ገለፃ ማድረግ፡<br>• ያዘጋጁትን መሥሪያ መሳሪያ አጠቃቀሙን ፡<br>• ለውሀ ቀለም ውሀ የቀለም ትሪ፣ የውሀ ቀለም ፣ ብሩሽ፣ ወረቀት፣ ቀለም ፣ ማስደገፊያ፣… የመሳሰሉት እያዘጋጁ በኋላ ማድረግ።<br>• በተመሳሳይ የሌሎችንም የቀለማት አይነት እንደየባህሪያቸው ማስረዳትና እንዲያዘጋጁ ማድረግ።<br>• ተማሪዎቹ ቀለም ቅብ ሠርተው እንደሆነ፣ ወይም የሌሎቹን ሰዓሊያን ሲሰሩ አይተው እንደሆነ፣ ምን ምን እንዳዩ ፣ እንዴት ይሰሩ እንደነበር በመጠየቅ መጀመር፡<br>• የተማሪዎቹን ግንዛቤ መነሻ በማድረግ የአሰራር አይነቶችና ዘዴዎችን በስፋት ማስረዳት።<br>• ውሀ ቀለም አሠራርን ቅደም ተከተል ማስረዳት፡<br>• የውሀ ቀለም መሥሪያ መሣሪያዎችን ከሌሎች የቀለም ቅብ መሣሪያዎች የሚለዩበትን መግለጽ ፣እ ቃዎቹንም ማሳየት፡<br>• ቀለል ያሉ የቁሳቁስ ጥናት በውሀ ቀለም እንዲሰሩ ማድረግ፡<br>• የዘይት ቀለም የአቀባብ ቅደም ተከተልን ማስረዳት ፡<br>• ዘይት ቀለም በመሥሪያ ቁሳቁስም ሆነ በባህሪው ከውሀ ቀለም እንደሚለይ ማስረዳት፡ ለምሳሌ፡ / በብሩሽ ልስላሴና ጥንካሬ፣ በአበጣበጡ ፣ በውሀና |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | | በዘይት መሆኑ ፣ በአቀባብ ቅደም ተከተል ፣ ከንጣት ወደ ጥቁረትና ከጥቁረት ወደ ንጣት መሄዳቸው ፣ ለመድረቅ የሚወስድባቸው ጊዜ፣ በወረቀትና በሸራ፣ … ወዘተ ያላቸውን ባህሪይ መግለጽ፡<br>• የዘይት ቅብ ሥራዎች እንዲሰሩ ማድረግ<br>• የቴምፕራ አሰራርን በመግለጽ ከወሀ ቀለም ጋር የሚዛመድበትን ባህሪ መግለጽ። እንዲሁም ከዘይት ቀለም የአሰራር ባህርይ ጋር የሚያመሳስላቸውን በመግለጽ፡ በሁለቱ የአቀባብ ዘዴዎች መሀል ያለ መሆኑን መግለጽ። |

## ግምገማ

- የቀለም ቅብ መሥሪያ መሳሪያዎች ማዘጋጀታቸውንና መጠቀማቸውን በምልከታ ማረጋገጥ
- ስለ ቀለም ቅብ አይነቶች ባህርይና አሰራር መረዳታቸውን በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ፡ መሥራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ
- ስለ ቀለማት ድርሰት የሰሩትን በምልከታ ማረጋገጥ
- ስዕልን እንዴት መያዝና ጠብቀው ለረዥም ጊዜ ሳይበላሽ መያዝ እንደሚችሉ የተረዱትን በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ
- የሰሩዋቸውን ሥራዎች ለእይታ መብቃቱን በምልከታ ማረጋገጥ።

## የመማር ማስተማሪያ መሣሪያዎች

- ለቀለም ቅብ መሥሪያ መሳሪያዎች ፡ ብሩሽ፣ የውሀና የዘይት ቀለም ፣ ወረቀት፣ ካንቫስ ፣ ፓሌት /ቀለም ትሪ/፣ ውሀ ፣ ዘይት፣ ውሀ መያዣ፣ ስትራቶ፣ ቦርድ
- የውሀ ቀለም በጠጠር ፣በፈሳሽ ፣ በዱቄት፣ ዘይት ቀለም፣ ቴምፕራ ፣ ወረቀት ፣ ብሩሽ ካንቫስ፣ ውሀ ፣ ዘይት፣ ፓሌት የተሰሩ ስራዎች፣ ፖስተር ፣ ካለንደር
- ቀለማት ፣ ወረቀት ፣ ብሩሽ ፣ ቻርት
- ስዕልን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ፖርት፣ ፎልዮ፣ መደርደሪያ

## ምዕራፍ አራት ፡ ህትመት *(2 ክፍለ ጊዜ)*

***የምዕራፉ ዓላማዎች*:-** ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ

- የህትመት መሥሪያ መሳሪዎችን በስፋት ያውቃሉ
- የስቴንስል አዘገጃጀትን በተለያዩ ቀለማት የመሥራት ክህሎት ያዳብራሉ
- የባቲክ ህትመትእና የአስሮ ማቅለም አሠራርን ግንዛቤ ያዳብራሉ
- በሚሰሯቸው ሰራዎች ላይ በመነጋገር ለጥበቡ ፍቅርና እንክብካቤ ማድረግ እንዳለባቸው ያውቃሉ፡፡

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| ተማሪዎች ይህን ይዘት ከተማሩ በኋላ<br>• በዚህ ደረጃ የሚጠቀሙበት የህትመት መሥሪያ መሣሪያዎችን ይለያሉ፡፡<br>• ለህትመት ሥራ የሚጠቀሙባቸውን ቴክኒክ ደረጃ በደረጃ እያሳደጉ ይጠቀማሉ፡፡ | 4.1 **የህትመት መሥሪያ መሳሪያዎች** /1 ክፍለ ጊዜ/<br>• የስቴንስል አዘገጃጀት | • የህትመት መሥሪያ መሳሪያዎች እንዲገልፁ በመጠየቅ የእለቱን ትምህርት መጀመር፡<br>• በቀጣይነት በዚህ ክፍል ደረጃ ባለፈው ከተማሩት ትምህርት ተጨማሪ የሆኑ አሰራሮችንና መሥሪያ መሳሪያዎችን ማስተዋወቅ፡<br>• በመሥሪያ መሳሪያዋቹ እንዴት እንደሚጠቀሙ ማስረዳት፡፡<br>• የስቴንስል አዘገጃጀትን ደረጃ በደረጃ እያሳደጉና እያሰፉ መጠቀም መቻላቸውን በመጠየቅ እንዲያስረዱ ማድረግ፡<br>• የተረዱትን በክፍል ውስጥ ውይይት እንዲያደርጉበት ማድረግ፡፡ |
| • ለሶስት ቀለም የህትመት አሰራር የሚጠቀሙበትን የስቴንስል አዘገጃጀት ቅደም ተከተል ይናገራሉ፡፡<br>• እስቴንስልን በተግባር ይለማመዳሉ፡፡<br>• የባቲክ ህትመትን ይሰራሉ፡፡<br>• ለባቲክ መሥሪያ መሳሪያዎች የሆኑትን ይለያሉ፡፡ | 4.2 **የ3 ቀለም ህትመት ስቴንስል አዘገጃጀትና አሰራር**/1 ክፍለ ጊዜ/<br>• የባቲክ ህትመት | • ለሶስት ቀለምም ህትመት የሚሆኑ የስቴንስል አዘገጃጀትን ማስረዳት፡<br>• ለህትመት ያዘጋጁትን ስቴንስል ሰርተው ለህትመት ካዘጋጁ በኋላ ከቀላል ቀለም ወደ ከባድ ቀለም መጠቀም እንዳለባቸው ማስረዳት፡<br>• ስቴንስሉን ከተጠቀሙበት በኋላ በንጽህና በመያዝ ለቀጣይ ህትመት ዝግጁ አድርገው በንጽህና መያዝ እንዳለባቸው ማስረዳት፡<br>• በመቀጠልም የባቲክ ህትመት አሰራር ዘዴዎችን ገለፃ ማድረግ ፡<br>• የአስሮ ማቅለም ዘዴን ፣ የመንከርን፣ በሻማ በመዝጋት ፣ የማተም /የማቅለም/ ፣ዘዴን በስፋት ማስረዳት፡<br>• የሰሩትንም ሥራ ወደ ክፍል አምጥተው እንዲሳዩ ማድረግ፡፡ |

**ግምገማ**

- የህትመት መሥሪያ መሳሪያዎችን መዘርዘራቸውን በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ፡
- የስቴንስል አዘገጃጀትን በተረዱት መሠረት መስራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፡

- የሶስት ቀለም ህትመት ስቴንስል አዘገጃጀት አሠራርና መረዳታቸውን መሥራት መቻላቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፡
- የባቲክ ህትመት አሰራር ዘዴዎችን መገንዘባቸውን በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ፡

## የመማሪያ ማስተማሪያ መሣሪያዎች

- የህትመት መስሪያ መሣሪያዎች የሆኑትን ወረቀት፣ ምላጭ /ከተር/ ፣ቀለም ፣ ሀር ፣ጨርቅ ፣ፓሌት፣ ባሊ ፣ውሀ፣ ስፖንጅ፣ ሻማ እሳት ብሩሽ …
- የተሰሩ ስራዎችን ማሳየት መፃህፍት
- ወረቀት፣ ቀለም፣ ጭላጭ /ከተር /፣ ስፖንጅ ፣ የሚታተምበት አካል ፣ /ወረቀት ፣ መስተዋት ፣ ጨርቅ፣ ቲሸርት…/፣ እርሳስ ፣ ላጲስ፣
- ለባቲክ ህትመት የምንጠቀምባቸው ባሊ፣ ውሀ፣ ቀለም፣ ገመድ፣ ጨርቅ፣ ሻማ ፣ እሳት፣ ብሩሽ መስቀያ፣

## ምዕራፍ አምስት፡ ኪነ ጽህፈት *(2 ክፍለ ጊዜ)*

***የምዕራፉ ዓላማዎች:-*** ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ

- *መሠረታዊ የመስመር አጣጣልን ያውቃሉ*
- *ፊደላትን በተለያዩ መሥሪያ መሳሪያዎች ተጠቅመው መሥራትን ያውቃሉ*
- *ፊደላትንም ሆነ ቁጥሮችን በብርሀንና ጥላ መሥራትን ያውቃሉ*
- *የተለያዩ ኢንፎርሜሽን ፖስተሮችን፣ መሪ ፖስተሮችን፣ … መሥራትን ያዳብራሉ።*

| *የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘት* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ይዘት ከተማሩ በኋላ*<br>• ኪነ ጽህፈትን ለመማር መሠረታዊ የሆነውን የመሥመር አጣጣልና የፊደሉን ቅርጽ መለየት አስፈላጊ መሆኑን ይናገራሉ።<br>• ፊደላትን በብሩሽ ፣በማርከር፣ በመንጎል፣ በመፃፍ ድርብ ፊደል አፃፃፍን ይለማመዳሉ። | **5.1. መሠረታዋ መስመር አጣጣል**<br>*/1 ክፍለ ጊዜ/*<br>• ፊደላትን በተለያዩ መሳሪያዎች መፃፍ፡<br>• በብሩሽ<br>• በማርከር<br>• በማንጎል<br>• በኮምፓሶችና ማስመሪያዎች … | • መሠረታዊ የመስመር አጣጣልን እንዲገልፁ በመጠየቅ መጀመር<br>• መሠረታዊ የመስመር አጣጣል ለምን እንደሚጠቅም በመግለጽ በፊደላቱ ቅርጽና አወቃቀር የተነሳ ለአንዱ ፊደል የምንጠቀምበት ስትሮክ ከሌላው የፊደል ስትሮክ ልዩነት እንዳለው ማስረዳት።<br>• ፊደላትን በድርብ ጽሁፍ ለመለማመድ በተለያዩ የጽህፈት መሳሪያዎች በመጠቀም ልምምድ ማድረግ እንደሚችሉ ይረዳሉ፡<br>• በብሩሽ ፊደላትን በመፃፍ መለማመድ፡<br>• በማርከር ፊደላትን በመፃፍ መለማመድ፡<br>• በማንጎል ፊደላትን በመፃፍ መለማመድ እንዲችሉ ማድረግ፡<br>• በኮምፓሶችና በተለያዩ የጽህፈት መሣሪያ መሳሪያዎች። |
| የተለያዩ አይነት ፖስተሮችን<br>• በማህበራዊ ጉዳዮች<br>• በጤና ችግሮች | **5.2. ፊደላትና ቁጥርን በብርሀንና ጥላ**<br>*/1 ክፍለ ጊዜ/*<br>• ፖስተር | • የተለማመዱዋቸውንና የሰሯቸውን ፊደላት /ቁጥር/ በብርሀንና ጥላ መሥራት መቻላቸውን ማስረዳት፡ |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| • በትራፊክ ደህንነት የመሳሰሉትን በስዕል /ፖስተር/ ይሰራሉ። | • ልማት<br>• የአካባቢ ንጽህና<br>• ተላላፊ በሽታዎች H.I.V. Aids<br>• ወባ | • የሚጽፏቸውን ፊደላት በድርብ ጽሁፍ በማድረግ ብርሀን ሲያርፍበት የሚፈጥረውን በአካሉ ላይ ሆነ በወዳቂ ጥላው የሚኖረውን ስሜት እየሰሩ እንዲለማመዱ ማድረግ።<br>• በከተማዎች ውስጥ የተለያዩ የበዓላት፣ የጤና፣ የንግድ ምልክት፣ ወዘተ… ፖስተሮች ማየታቸውን በመግለጽ የሚያስታውሱትን ፖስተር እንዲገልፁና እንዴት እንደተሰራ የተረዱትን እንዲገልፁ በመጠየቅ መጀመር፡<br>• ፖስተር ከቀለም ቅብ ድርሰት ከሌሎች የሚለይበትን መሠረታዊ ባህሪይ ጠቅለል ባለ መልኩ መግለጽ እንደሚያስችለን ማስረዳት፡<br>• ፖስተር በቀላሉ ወደ ማህበራዊ ህይወታችን ሰዎች ሁሉ ገጠር ከከተማ ሊረዳው የሚችል ሀሳብ ማስተላለፊያ ዘዴ መሆኑን ግንዛቤ ማስያዝ፡<br>• በተግባር እየሰሩ እንዲለማመዱ ማድረግ፡ ማህበራዊና ተላላፊ በሽታዎችን በፖስተር አሰራር<br>• በክበባት ደረጃ ማደራጀት። |

## ግምገማ

- መሠረታዊ የመስመር አጣጣልን መስራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ
- ፊደላትን የተለያዩ መሥሪያ መሣሪያዎች ተጠቅመው መፃፍ መቻላቸውን በምልከታ ማረጋገጥ
- በፊደላት ላይ / በቁጥር ላይ በብርሀንና ጥላ እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ በምልከታ ማረጋገጥ
- የተለያዩ ፖስተሮችን መሥራት መቻላቸውን በምልከታ ማረጋገጥ።

## የመማሪያ ማስተማሪያ መሣሪያዎች

- እርሳስ ፣ ላጲስ፣ ምላጭ /ከተር/
- ብሩሽ ፣ማርከር ፣ማንጎል ፣ ኮምፓስ ፣ማስመሪያ
- ማስመሪያ ፣እርሳስ ፣ላጲስ ፣ምላጭ /ከተር/ ብሩሽ፣ ወረቀት፣ ቦርድ ፣…
- ቀለም ፣እርሳስ ፣ላጲስ፣ ምላጭ /ከተር/ ፣ብሩሽ፣ ወረቀት፣ ማስማሪያ፣ ኮምፓስ ፣ፓሌት፣ የተለያዩ ፖስተሮች፣ ፓምኘሌት፣ መጋዚን

## ምዕራፍ ስድስት፡ ቅርፃ ቅርጽ *(2 ክፍለ ጊዜ)*

***የምዕራፉ ዓላማዎች***:- ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ

- ሶስት  አውታረ መጠን ቅርጽን ለመሥራት የሚያስፈልጉ ቅደም ተከተልን ያውቃሉ
- በጭቃ ሶስት አውታረ መጠን ያለው ቅርጽ መሥራትን ያውቃሉ
- በጭቃ ከሰሩት ቅርጽ ላይ ኔጌቲቭ እንዴት እንደሚያዘጋጁ ይለያሉ
- ያዘጋጁትን  ኔጌቲቭ ወደ ጂሶ /ሲሚንቶ/  በመቀየር ፖዘቲቭ/ ማዘጋጀትን ያውቃሉ
- ወደ ፖዘቲቭ የተቀየረውን ቅርጽ ከኔጌቲቭ በማለያየት /በመፈልፈል/ የሚፈለገውን ቅርፅ ማውጣትን ያውቃሉ፣
- ቅርፃ ቅርጽ ስራን በራስ ፈጠራ እየሰሩ የተለያዩ ሞዴሎችን መሥራት ይችላሉ።

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| ተማሪዎች ይህን ይዘት ከተማሩ በኋላ<br>• ለቅርፅ መሥሪያ የሚያስፈልገውን ስታንድ እንዴት እንደሚያዘጋጁ፣ ከምን እንደሚያዘጋጁ በስፋት ይዘረዝራሉ።<br>• በጭቃ ሶስት አውታረ መጠን ቅርፅን ይሰራሉ።<br>• በጭቃ የሰሩትን ቅርፅ እንዴት ወደ ኔጌቲቭ መቀየር እንዳለባቸው ያውቃሉ።<br>• ያዘጋጁትን ኔጌቲቭ ላይ በመሙላት ወደ ፖዘቲቭ እንዴት እንደሚቀይሩት ያውቃሉ።<br>• ሞልተው ያዘጋጁትን በመፈልፈል ዋናውን ምስል ማውጣት መቻላቸውን ያውቃሉ። | **6.1. ባለ ሶስት አውታረ መጠን የቅርጽ አሰራር ቅደም ተከተል**<br>/2 ክፍለ ጊዜ/<br>• ከጭቃ ሶስት አውታረ መጠን ቅርፅ/መጠናቸው ከ30 ሴ.ሜ. ያልበለጠ /<br>• የኔጌቲቭ አዘገጃጀት<br>• ኔጌቲቭን ወደ ጂሶ /ሲሚንቶ/ መቀየር ፖዘቲቭ<br>• መፈልፈልና መጨረስ | • ቅርጽን በሶስት አውታረ መጠን ለመሥራት የምንጠቀምበት ስታንድ እንዴት እንደሚዘጋጅ ተማሪዎቹ እንዲያስረዱ ማድረግ፣<br>• የተማሪዎቹን ግንዛቤ መነሻ በማድረግ፣ በወፍራም ጣውላ ላይ ወፍራም ሽቦ /ቀጠን ያለ ፌሮ/ በማዋቀር እንዳይነቃነቅ ካደረጉ በኋላ ወደላይ ያለውን አካል እንደ ቅርፁ እንቅስቃሴ መጠን እንደ አስፈላጊነቱ በሽቦና በእንጨት በማወቀር መሥራት መቻላቸውን ማስረዳት ። ስታንዱን አዘጋጅተው ሲጨርሱ ጭቃ በመሙላት ከአጠቃላይ ቅርፁ ወደ አጨራረሱ በመሄድ መስራት መቻላቸውን ማስረዳት።<br>• በጭቃ ሶስት አውታረ መጠን የሆነ ቅርፅ እየሰሩ እንዲለማመዱ የስታንድ አዘገጃጀትን በተረዱት መሠረት እንደሚፈልጉት የቅርጽ አይነት ለይተው እንዲያዘጋጁ ማድረግ። ባዘጋጁት ስታንድ ላይ ደረዳ በደረጃ ቅርፁን ተከትለው ጭቃውን እየሞሉ እየጨረሱ እንዲሄዱ ማድረግ። የጭቃውን ርጥበት ለመጠበቅ የሚወስደውን ጥንቃቄ እንዳይዘነጉ ክትትል ማድረግ።<br>• የሰሩትን የጭቃ ሞዴል ወደ ኔጌቲቭ እንዴት እንደሚቀይሩ ደረጃ በደረጃ በቆርቆሮ ከመከፋፈል አንስቶ ጂሶ ረጭቶ በእንጨት ጆንያ በማጠናከር መጨረስን ማስረዳት፣<br>• ካስት የተደረገውን ኔጌቲቭ እንዴት እንደሚከፍቱትና ለፖዘቲቭ እንዴት እንደሚያዘጋጁ ማስረዳት።<br>• ከፍተው ያዘጋጁትን ኔጌቲቭ እንዴት እንደሚገጥሞትና ለመሙላት ማዘጋጀት እንዳለባቸው ማስረዳት፣ |

| የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች |
|---|---|---|
| | | • ገጥመው ያዘጋጁትን ኔጌቴቭ ለመሙላት አመቺ አድርገው እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣<br>• ጄሶውን ወይም ሲሚንቶውን በጥብጠው ማዘጋጀት እንዳለባቸውና ወደ ኔጌቴቩ በመጨመር ዋናውን ስራ ማዘጋጀታቸውን ማስረዳት፣<br>• እስኪደርቅ መጠበቅ እንዳለባቸው በመግለጽ ለቀጣዩ ሂደት እንዲዘጋጁ ማድረግ።<br>• በኔጌቴቭ ውስጥ ሞልተው ያዘጋጁትን ጄሶ /ሲሚንቶ/ መጠንከሩንና ለመፈልፈል አመቺ መሆኑን ካዩ በኋላ ከላይ ካለው ጆንያ በመጀመር ደረጃ በደረጃ በመፈልፈል ፖዘቲቩን ሳይበላሽ ማውጣትና እንዲደርቅ በማድረግ ስፓቴና ዝግጁ ማድረግ መቻላቸውን ማስረዳት። |

## ግምገማ

- ስለ ሶስት አውታረ መጠን  አሠራርና ቅደም ተከተል የተረዱትን በጥያቄ ማረጋገጥ
- ሶስት አውታረ መጠን ቅርጽ ያለው ቅርፅ መሥራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ
- ኔጌቴቭ ለማዘጋጀት የተጠቀሙበትን ቁስና አጠቃቀማቸውን ቅደም ተከተሉን ጠብቀው ማዘጋጀታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ
- ፖዘቲቭ ሲያዘጋጁ መጠቀም ያለባቸውን ነገሮች በአግባቡ መጠቀማቸውን መከታተል
- ሞልተው ያዘጋጁትን ቅርፅ ኔጌቴቩን  በመፈልፈል ተፈላጊውን ቅርፅ በማውጣት ማዘጋጀት መቻላቸውን መከታተል
- የተለያዩ ሞዴል ሥራዎችን በራስ ፈጠራ ታግዘው መለማመዳቸውን በምልከታ ማረጋገጥ።

## የመማር ማስተማሪያ መሣሪያዎች

- የቅርፅ መሥሪያ ስታንድ ለማዘጋጀት ወፍራም ጣውላ ፣ ሽቦ፣ ሚስማር ፣ጉጠት ፣ሽፍሻፊ እንጨት፣ ጭቃ፣ ላስቲክ፣ ጨርቅ ፣መዶሻ፣ ...
- በተዘጋጀው ስታንድ ላይ የተዘጋጀውን ጭቃ እያደረጉ መስራት ጭቃውን ለማስተካከል የቅርጽ መሥሪያ ቱልሶችን ፣የእንጨት የሽቦ፣ የብረት መስሪያዎችን፣ ጨርቅና ላስቲክ ማሰሪያ ገመድ፣ ...
- ኔጌቴቭ ለማዘጋጀት ስስ የተቆራረጠ ቆርቆሮ ፣ጄሶ፣ጆንያ  ፣ውሀ መበጥበጫ ሳህን፣ ማጠናከሪያ እንጨት/ጣውላ/ ፣እንግሊዝ ጨው/ቅባት/፣ ብሩሽ፣ መሮ
- ፖዘቲቭ  ለማዘጋጀት ጆንያ ፣ማጠናከሪያ ጣውላ ፣ጄሶ /ሲማንቶ/፣ ወሀ መበጥበጫ ሳህን፣
- ለመፈልፈል የምንጠቀምባቸው ቁሳቁስ መሮ፣ ጉጠት፣ መዶሻ
- ከሀሳብ አፍልቀን ለምንሰራው ስራ ስታንድ ፣ጭቃ ፣ጭቃማስተካከያ ቱልስ፣ የእንጨት፣ የሽቦ /ብረት/

## ምዕራፍ ስምንት: ኮምፒዩተር ግራፊክስ *(4 ክፍለ ጊዜ)*

***የምዕራፉ ዓላማ፡-*** ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ

- ስለ ኮምፒዩተር ምንነትና ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ
- ስለ ኮምፒዩተር ጥበብና አሰራር ይናገራሉ
- በኮምፒዩትር ተጠቅመው ዲዛይን የመሥራትን ባህል ያዳብራሉ።

| *የሚጠበቅ አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ* | *ይዘት* | *የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ይዘት ከተማሩ በኋላ*<br>• ስለ ኮምፒዩተር ምንነትና ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ።<br>• ስለ ኮምፒዩተር ጥበብና አሰራር ይናገራሉ<br>• ኮምፒዩተር በመጠቀም ምስሎችን ቀርፀው ያሳያሉ።<br>• የፊልምና የፎቶ ቅንብርን ሠርተው ለእይታ ያቀርባሉ። | 8.1. **የኮምፒዩተር ምንነትና ጠቀሜታ** */1 ክፍለ ጊዜ/*<br><br>8.2. **በኮምፒዩተር ጥቁርና ነጭ** */3 ክፍለ ጊዜ/*<br>• ስዕሎችን<br>• ዲዛይኖችን መስራት<br>• የሰራቸውን የህትመት<br>• የቀለም ቅብ<br>• ሥራዎችን አትሞ ማውጣት። | • ተማሪዎች ስለ ኮምፒዩተር ጥበብ እንዲናገሩ እድል መስጠት፡<br>• መምህሩ ስለ ኮምፒዩተር ምንነትና አጠቃቀም ገለፃ መስጠት።<br><br>• በኮምፒዩተር እንዴት መጠቀም እንደሚቻል የኮምፒዩተሩን ክፍሎችና ተግባራት በቅደም ተከተል ማሳየት። በመቀጠልም የእንግሊዝኛና የአማርኛ ፊደላት አፃፃፍን ፡ ፊደላትን የተለያዩ ቅርጾችና መጠኖች እንዳሏቸው ፡ እንዲሁም ስዕሎችን የተለያዩ የመጠቀሚያ ቁሳቁስ፣ አልባሳት፣ ቤቶች ዲዛይኖችን እንዴት ወደ ኮምፒዩተር ውስጥ ማስገባትና በተለያየ መጠን አትሞ ማውጣት እንደሚቻል ማሳየት።<br>• በኮምፒዩተር ውስጥ ባለው ኘሮግራም በመታገዝ /ኮላር ድሮው/ ወዘተ.. ዲዛይኖችን መስራት እንደሚቻል ማሳየት። እነሱም በነዚህ ዘዴዎች በመታገዝ የተለያዩ ዲዛይኖችን በቡድን ሠርተው እንዲያመጡ የቤት ሥራ መስጠት። |

### ግምገማ

- ተማሪዎቹን ስለ ኮምፒዩተር ጥበብና እንዲሁም ጥቅም እንዲዘረዝሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ
- ስለ ኮምፒዩተር አሰራር ቴክኒክ እንዲናገሩ እድል መስጠት
- ኮምፒዩተሩን ተጠቅመው ምስል በቡድንና በግል ሲቀርፁ በምልከታ ማረጋገጥና ተገቢውን እርማት መስጠት

### የመሥሪያ ማስተማሪያ መሣሪያዎች

- ኮምፒዩተር ፣ ወረቀት ፣ የኮምፒዩተር ቀለም ማተሚያ